MONTCLAIR SCHOOL
OF ACADEMICS & ENRICHMENT

# የሞንትክሌር ት/ቤት የአቴንዳንስ ፖሊሲ
## የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
የትምህርት ዘመን 2025-2026

በሞንትክሌር ተማሪዎቻችን በትምህርታቸው ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ህይወታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ የማድረጉ ኃላፊነት እንደ መሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት የጋራ ኃላፊነታችን ነው። የተማሪዎቻችንን ስኬት የማረጋገጥ አንዱ ወሳኝ አካል ተማሪዎቻችን በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጡ የሚከለክሏቸውን መሰናክሎች መለየት እና ማስወገድ ነው። **ጠንካራ አቴንዳንስ እያንዳንዱ ተማሪ በማህበራዊ፣ በስሜታዊ እና በትምህርታዊ ዘርፎች የጎለበተ እንዲሆን ይረዳል።** የአንድ ተማሪ ጠንካራ አቴንዳንስ ያንን ግለሰብ ተማሪ ብቻ ሳይሆን የክፍል ጓደኞቻቸውን፣ መምህሮቻቸውን እና ሰፊውን የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ወጥነትን እና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ይረዳል።

አቴንዳንስ ገና በለጋ ዕድሜ ላይ አስፈላጊ ነው። ልማዶች ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በገቡ በአንደኛው ዓመት ውስጥ ይመሠረቱና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሞላ አንድ ዓይነት የመሆን አዝማሚያ አላቸው። ተማሪዎች መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገቡበት ጊዜ የአቴንዳንስ ክፍተቶች መስፋት ይጀምራሉ።

ሁሉም ያመለጡ ትምህርቶች፣ ከትምህርት ቤት የመቅረቱ ምክንያቶች ምንም ቢሆኑ ምንም፣ የተማሪ ስኬት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በዚህ ምክንያት፣ DPS **ሥር የሰደደ ወይም ተደጋጋሚ ከት/ቤት መቅረትን** በመቀነስ ላይ ያተኩራል። ***ሥር የሰደደ ወይም ተደጋጋሚ ከት/ቤት መቅረት፦*** **በማንኛውም ምክንያት እና ያለምክንያት ከት/ቤት መቅረትን እና እገዳን ጨምሮ በትምህርት አመት ከተመዘገበው ጊዜ ቢያንስ 10 በመቶ መቅረት ነው።** ትኩረቱ በአቴንዳንስ ምክንያት በሚያመልጥ ትህርት ምክንያት በትምህርት እና በማህበራዊ ስሜታዊ ትምህርቶች ላይ በደርስ ተጽእኖ ነው።

ሥር የሰደደ ቀሪነት እና የአቴንዳንስ ምጣኔ ሲሰላ፣ የትምህርት ቀኑ እያንዳንዱ ደቂቃ ይቆጠራል። ይህ ማለት ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ዘግይቶ ሲደርስ ወይም ከትምህርት ቀድሞ ሲወሰድ የሚያመልጠው የክፍል ደቂቃዎች የተማሪው ቀሪነት እና አቴንዳንስ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።

እያንዳንዱን ተማሪ ቀኑን ሙሉ፣ በየቀኑ በትምህርት ቤት እንፈልጋለን!

የአካዳሚክ አፈፃፀምን ለማሻሻል እና ለኮሌጅ እና ለስራ እድሎች ዝግጁ ለመሆን ተማሪዎች በሰዓቱ መገኘት እና ለሁሉም ክፍሎች በየቀኑ መቆየታቸው አስፈላጊ ነው።

- በኮሎራዶ ውስጥ ያሉ ልጆች ከ4 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይበረታታሉ።
- በኮሎራዶ ውስጥ ያሉ ሁሉም ልጆች በአጠቃላይ ከ4 እስከ 16 ዓመት እድሜ ያላቸው ልጆች በት/ቤት መማር አለባቸው።
- የDPS ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከሰኞ እስከ አርብ ይከታተላሉ።
- የDPS የትምህርት ዓመታት በኦገስት ይጀምርና በሜይ ወይም ጁን ውስጥ ያበቃል።
- ልጅዎ ከትምህርት ቤት ሲቀር፣ ለትምህርት ቤቱ የእንግዳ ተቀባይ ቢሮ ማሳወቅ አለብዎ።
- የሞንትክሌር ት/ቤት የትምህርት ዘመን አቆጣጠር በድረገጻችን ይገኛል።

በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአቴንዳንስ ግብ ወይም ኢላማ አለው። የሞንትክሌር የ2025-26 የትምህርት ዘመን አቴንዳንስ ኢላማ 95 በመቶ ነው።

**<u>የወላጅ/አሳዳጊ ሚና በአቴንዳንስ</u>**

ወላጆች ልጃቸው ለስኬታማነት መዘጋጀቱን እና ክፍል እየተከታተለ መሆኑ/ኗን ለማረጋገጥ የሚረዱ አሰራሮች አሉ።

- ልጅዎ በሚዘገይበት፣ ቀደም ብሎ በሚወጣበት ወይም በሚቀርበት ጊዜ ሁሉ ከትምህርት ቤቱ ጋር ይነጋገሩ።
- ቀጠሮዎችን ከትምህርት ቤት በኋላ ወይም ምንም ክፍሎች በሌሉባቸው ቀናት ይያዙ።
- የእረፍት ጊዜዎችን እና ጉዞዎችን ትምህርት በሌለበት ቀናት ያቅዱ።
- የሆነ ነገር ከተፈጠረ ልጅዎን ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣት የመጠባበቂያ እቅድ ያዘጋጁ።
- ልጅዎ ጤናማ ልማዶች እንዳለው ያረጋግጡ።
    - በሰዓቱ መተኛት፣ በቂ እንቅልፍ መተኛት እና በጊዜ መንቃት።
    - ከአንድ ምሽት በፊት ልብሶችን እና ቦርሳዎችን ያሰናዱ።
    - የልጅዎን ጤንነት ይጠብቁ፣ እንዲሁም ልጅዎ የሚፈለጉትን ክትባቶች የወሰዱ መሆኑን/ኗን ያረጋግጡ።
- ልጅዎ ስለ ትምህርት ቤት የተጨነቀ መስሎ ከታየ፣ አስተማሪዎችን ወይም የትምህርት ቤቱን አማካሪ ያነጋግሩ።
- በወላጅ ፖርታል ላይ የተማሪዎን አቴንዳንስ ይከታተሉ።

ወደ ጠንካራ አቴንዳንስ የሚያመሩ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ለማዘጋጀት በሚወስዷቸው እርምጃዎች ላይ ተጨማሪ መረጃን ከአቴንዳንስ ስራዎች አደረጃጀት ማግኘት ይችላሉ።

- [ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት እና ለአጸደ ሕፃናት ቤተሰቦች ጠቃሚ ምክሮች]
- [ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች ጠቃሚ ምክሮች]
- [ለመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች ጠቃሚ ምክሮች]

**አቴንዳሶችን ሪፖርት ማድረግ እና መከታተል**

- ተማሪዎ እንደሚይቀር ወይም ዘግይቶ እንደሚመጣ በማሳወቅ ጊዜ ይቆጥቡ። የDPS ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በመንከባከብ ላይ እንዲያተኩሩ ኮምፒውተሮቻቸውን ወይም ስማርት ስልኮቻቸውን በመጠቀም ስለ ቀሪዎች ወይም ዘግይቶ መድረሶች ማወቅ ይችላሉ።
- ይህንን አዲስ ባህሪ ለመጠቀም የDPS ተማሪዎች አሳዳጊዎች/ወላጆች የሚሠራ የDPS የወላጅ ፖርታል መለያ (አካውንት) ሊኖራቸው ይገባል። ለመመዝገብ ወይም መለያዎ የሚሠራ እና ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ myportal.dpsk12.orgን ይጎብኙ። ይህን አዲስ ባህሪ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በመስመር ላይ መገኘትን ስለማስገባት ይማሩ።

**የፈቃድ ቀሪዎች**

በዴንቨር የህዝብ ትምህርት ቤቶች ቦርድ ፖሊሲ መሰረት፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና ርእሰ መምህሩ ሁለቱም ቀሪውን ከተቀበሉት ቀሪው ይቅርታ ሊደረግ ይችላል። ወላጅ/አሳዳጊ የተማሪውን መቀረት ያወቁት መሆናቸውን ለማሳወቅ እና ቀሪው ፈቃድ እንዲያገኝ ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው በቀረበት፣ ዘግይተው ወደ ትምህርት ቤት በደረሱ ወይም ቀደም ብለው በወሰዱ ቁጥር ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለበት።

በስቴት ህግ መሰረት፣ የሚከተሉት ቀሪዎች ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡-

- ጊዜያዊ ህመም ወይም ጉዳት (ተያያዥ ቀጠሮዎችን ጨምሮ)
- አካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ እክል ወይም ሁኔታ (ተያያዥ ቀጠሮዎችን ጨምሮ)
- ሃይማኖታዊ በዓላት
- የቅርቤተሰብ አባል ሞት
- የትምህርት ቤት አገልግሎት ቀሪዎች (በትምህርት ቤቱ መሪ የተፈቀደላቸው እና ቀድመው የጸደቁ በትምህርት ቤት ተግባራት ውስጥ በመሳተፍ ምክንያት የሚከሰቱ ቀሪዎች)
- ከት/ቤት በመታገድ ወይም በመባረር ምክንያት ቀሪዎች

በተጨማሪም፣ ሞንትክሌር በሚከተሉት ምክንያቶች ቀሪዎችን ይፈቅዳል፡-

- (ከቀጣይ ሕመም ወይም ሁኔታ ጋር ያልተያያዙ የጤና ምርመራዎችን ጨምሮ) የሕክምና ወይም የጥርስ ሕክምና ቀጠሮዎች

- በተማሪው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሀዘን፣ በተመጣጣኝ መጠን (በቅርብ ቤተሰብ ውስጥ ባይሆንም)
- የፍርድ ቤት ችሎቶች እና በፍርድ ቤት የታዘዙ ቀሪዎች
- ከቤተሰብ ቁጥጥር ውጪ የሆኑ <u>**ጊዜያዊ**</u> የትራንስፖርት ጉዳዮች (ለምሳሌ ዛሬ ጠዋት መኪና ተበላሽቷል፣ ዛሬ አውቶብስ እየሰራ አይደለም፣ ቤተሰብ በተለይ በበረዶ በብዛት በጣለበት የከተማው ክፍል ውስጥ ይኖራል እና ትምህርት ቤት ባይዘጋም መጓዝ አለመቻል)።
  - መጓጓዣ ለአቴንዳንስ ቀጣይነት ያለው እንቅፋት ከሆነ፣ አቴንዳንስ ቡድናችን ቀጣይነት ያለው እና ጊዜያዊ ያልሆኑ ቀሪዎችን መፈቀድ ከመቀጠል ይልቅ የቤተሰቡን ችግር ለመፍታት ይሰበሰባል።
- በየትምህርት ዓመቱ ለኮሌጅ ጉብኝቶች፣ አምስት (5) ቀናት ቀሪዎች። የኮሌጅ ጉብኝቶች እንደቀሪዎች ከመያዝ ይቅርታ እንዲደረግላቸው፣ በኮሌጅ ጉብኝቱ ውስጥ የመሳተፍ ማረጋገጫ በሁለት (2) ቀናት ውስጥ ለት/ቤቱ መቅረብ አለበት።
- በአንድ ትምህርት አመት ውስጥ ለቤተሰብ ንግድ ወይም ለዕረፍት፣ እስከ አምስት (5) ቀናት ቀሪዎች (ለምሳሌ ለእረፍት፣ በቤተሰብ ሰርግ ላይ ለመገኘት፣ በሃይማኖታዊ በዓላት ዙሪያ የሚደረጉ ተጨማሪ የጉዞ ቀናት፣ ከከተማ ውጭ የሚኖር ቤተሰብን ለመጎብኘት አንድ ቀን መቅረት፣ ወዘተ)።

ት/ቤቱ ለፈቀዳቸው ማንኛውም ቀሪዎች ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም። ነገር ግን፣ አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት አመት 10 ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ቀናትን በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም በአካል፣ በአእምሮ ወይም በስሜታዊ እክል ወይም ሁኔታ ከቀረ በኋላ፣ ሞንትክሌር ለቀጣይ ቀሪዎች ይቅርታ ከማድረጉ በፊት የህክምና ሰነድ ይጠይቃል። በተጨማሪም ተማሪው የጤና እቅድ እና/ወይም የሴክሽን 504 እቅድ ወይም IEP የብቁነት ውሳኔ ያስፈልገው/ጋት እንደሆነ ልንገመግም እንችላለን። ተማሪው አስቀድሞ የጤና እቅድ፣ የሴክሽን 504 እቅድ ወይም IEP ካለው፣ እቅዱ መስተካከል እንዳለበት ለማየት ቡድኑ እንደገና መሰብሰብ ሊያስፈልገው ይችላል።

<u>**በጣም መታመም ማለት ምን ያህል መታመም ነው?**</u>

| **በሚከተሉት ምክንያቶች ልጅዎን ቤት ያውሉ ወይም እንክብካቤ ይጠይቁ፦** | **የሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆንም እንኳ ልጅዎን ወደ ትምህርት ቤት ይላኩ፦*** |
|---|---|
| 100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት ካለው/ካላት | የአፍንጫ ፈሳሽ እና/ወይም ሳል ያለው መለስተኛ ጉንፋን ቢኖረውም/ቢኖራትም |
| ባለፉት 24 ሰዓቶች ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ | ያለ ትኩሳት፣ ያለ ዓይን ህመም ወይም የአይን |

| | |
|---|---|
| በላይ ጊዜ ካስታወከ/ች | ሽፋን መቅላት የዓይን እንባ ማፍሰስ ቢኖረውም/ቢኖራትም |
| የማያቋርጥ ሳል፣ የመተንፈስ ችግር ወይም የትንፋሽ እጥረት ወይም ከሳል ጋር ትኩሳት ካለው/ካላት | ቀላል የሆድ ህመም ቢኖረው/ቢኖራትም |
| ህመም ያላቸው የሚፈሱ መግል ያላቸው ሽፍታ/እብጠቶች፣ የተጋጡ ወይም የተላጡ የአካል ክፍሎች እና/ወይም ትኩሳት ካለው/ካላት | ሌሎች ምልክቶች የሌሉት ቀለል ያለ ሽፍታ ቢኖረው/ቢኖራትም |
| የዓይን እብጠት፣ የዓይን ሕመም፣ የማየት ችግር ወይም የዓይን ጉዳት ካለው/ካላት | የጸጉር ቅማል ቢኖረው/ቢኖራትም። የሚያናድዱ/የሚያስጠሉ እና መታከም ያለባቸው ቢሆንም ቅማል ልጅን ከትምህርት ቤት ለማስቀረት ወይም ለማግለል ምክንያት አይሆኑም። |
| የምራቅ መዥረብረብ፣ የመዋጥ ችግር ወይም ትኩሳት እና/ወይም ሽፍታን ያስከተለ የጉሮሮ መቁሰል ካለው/ካላት | ሌሊቱን ትኩሳት ካልነበራቸው እና በዚያ ጊዜ ውስጥ ትኩሳትን የሚቀንስ መድሃኒት ካልወሰደ/ካልወሰደች |

**ልጅዎን ወደ ትምህርት ቤት መላክ እንዳለብዎ ወይም እንደሌለብዎ ካላወቁ ወይም ስለልጅዎ ጤና የተለየ ስጋት ካለዎ፣ የልጅዎን የጤና ሃኪም ወይም ጤና አገልግሎት ሰጪን፣ የአካባቢ አስቸኳይ ጊዜ ህክምና ሰጪን ወይም የትምህርት ቤቱን ነርስን ያነጋግሩ።*

**<u>ያለተፈቀዱ ቀሪዎች</u>**

ያልልተፈቀዱ ቀሪዎች <u>በወላጅ</u> /አሳዳጊ <u>እና</u> በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር/ት (ወይም ርእሰ መምህሩ የወከለው ሰው) ያልተፈቀዱ ቀሪዎች ናቸው። አንድ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ለት/ቤቱ ሳያስፈቅድለት አርፍዶ ሲመጣ ወይም ቀደም ብሎ ሲወጣ ያመለጠው ጊዜ ምክንያት እንደሌለው ቀሪ ይቆጠርበታል።

**<u>ማርፈድ</u>**

ትምህርት ከመጀመሪያው ጊዜ በኋላ እና በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ 50 በመቶው ጊዜ ውስጥ ወደ ክፍል የመጣ ተማሪ አርፋጅ ተደርጎ ይያዛል። በታቀደለት የትምህርት ቀን ከ50 በመቶ በላይ ያልተከታተለ ተማሪ ለዚያ ሙሉ ጊዜ እንደ ቀሪ ይቆጠራል።

**DPS የመጀመሪያ ደረጃ:**

ልጅዎን በሰዓቱ ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት **<u>ዋጋ አለው</u>!**

የሚከተሉትን ያውቃሉ?

| በትምህርት አመት ውስጥ፣ ልጅዎ በየቀኑ በ... የሚዘገይ ከሆነ | ልጅዎ በግምት... ትምህርት አምልጦታል | እንዲሁም በግምት .... አምልጦታል |
|---|---|---|
| 5 ደቂቃዎች | 2.5 የትምህርት ቀናት | 15 ትምህርቶች |
| 10 ደቂቃዎች | 5 ትምህርት ቀናት | 29 ትምህርቶች |
| 15 ደቂቃዎች | 7.7 የትምህርት ቀናት | 44 ትምህርቶች |
| 20 ደቂቃዎች | 10.3 የትምህርት ቀናት | 58 ትምህርቶች |
| 30 ደቂቃዎች | 15.5 የትምህርት ቀናት | 88 ትምህርቶች |

ጠንካራ አቴንዳንስን ለማስቀጠል እና በአካዳሚክ መንገድ ላይ ለመቆየት ልጅዎ በሰዓቱ መድረሱን ያረጋግጡ!

**ያስታውሱ፡- ቀሪ = የባከኑ ወይም ያመለጡ እድሎች**

**DPS ሁለተኛ ደረጃ (6 -12)፡-**

**ልጅዎን በሰዓቱ ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት <u>ዋጋ አለው</u>!**

የሚከተሉትን ያውቃሉ?

| በትምህርት አመት ውስጥ፣ ልጅዎ በየቀኑ በ... የሚዘገይ ከሆነ | ልጅዎ በግምት... ትምህርት አምልጦታል | እንዲሁም በግምት .... አምልጦታል |
|---|---|---|
| 5 ደቂቃዎች | 2.3 የትምህርት ቀናት | 15 ክፍሎች |
| 10 ደቂቃዎች | 4.7 የትምህርት ቀናት | 29 ክፍሎች |
| 15 ደቂቃዎች | 7 ትምህርት ቀናት | 44 ክፍሎች |
| 20 ደቂቃዎች | 9.5 የትምህርት ቀናት | 58 ክፍሎች |
| 30 ደቂቃዎች | 14 ትምህርት ቀናት | 88 ክፍሎች |

ጠንካራ አቴንዳንስን ለማስቀጠል እና በአካዳሚክ መንገድ ላይ ለመቆየት ልጅዎ በሰዓቱ መድረሱን ያረጋግጡ!

**ያስታውሱ፡- ቀሪ = የባከኑ ወይም ያመለጡ እድሎች**

**<u>የረጅም ጊዜ ቀሪዎች</u>**

ለረጅም ጊዜ መቅረት በሚከተሉት ይገለጻል፡-

- አስር ቀናት ወይም ከዚያ በላይ መቅረት፤
- የታወቀ ወደ ትምህርት ቤት የመመለሻ ቀን ያለው፤
- ትምህርት ቤቱ ተማሪው የት እንደሚሄድ ሲያውቅ፣ እና
- ተማሪው በማይኖርበት ወይም በቀረበት ጊዜ የትምህርት አገልግሎት አያገኝም።

እነዚህ ለምሳሌ ወደ ትምህርት ቤት የሚመለሱበት ቀን የሚታወቅ ከሀገር ውጭ ጉዞ ወይም ከቀዶ ጥገና ህክምና በኋላ የሆስፒታል ቆይታን ሊያካትቱ ይችላሉ። አንድ ተማሪ ለረጅም ጊዜ በመቀረበት ወቅት፣ ሞንትክሌር በDPS አሰራር መሰረት በገጽ-ለ-ገጽ ወይም በአካል የሚሰጠውን ትምህርት ለመተካት የመስመር ላይ ትምህርትን ወይም የማካካሻ ስራዎችን አይሰጥም።

በዚህ ጊዜ፣ ተማሪው ከሞንትክሌር እንዲወጣ ይደረግና እንደተመለሰ ወዲያውኑ እንደገና ይመዘገባል።

**<u>የማካካሻ ስራዎች</u>**

ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪዎቻቸው እንደሚቀሩ ካወቁ፣ በተቻለ ፍጥነት ለሞንትክሌር ሊያሳውቁ ያስፈልጋል። ከተቻለ የክፍል አስተማሪዎች እስከ አምስት (5) ቀናት ለቀረ ተማሪ የማካካሻ ስራዎችን ያዘጋጃሉ። ለአስር (10) ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ከትምህርት ገበታቸው ለቀሩ ተማሪዎች የማካካሻ ስራዎች አይሰጡም። ተማሪዎች ሙሉ ክሬዲት ለማግኘት ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ በሌሉበት ጊዜ ያመለጣቸውን ትምህርት የማካካሻ ስራዎች እና በቀሩበት ጊዜ መግባት የነበሩ ስራዎችን ለማስገባት አምስት (5) ቀናት አላቸው።

ምንም እንኳን እያንዳንዱ ተማሪ በቀሩበት ጊዜ ያመለጣቸውን ትምህርታቸውን እንዲያካክሱ ለመርዳት የተቻለንን ሁሉ ብናደርግም፣ አቴንዳንስ የተማሪውን ትምህርት በቀጥታ ይነካል። የማካካሻ ስራዎች በአካል የሚገኝን የትምህርት ተሞክሮ ሙሉ በሙሉ መተካት አይችልም።

**<u>አቴንዳንስን ለመደገፍ የሞንትክሌር አሠራር</u>**

በሞንትክሌር፣ ለጠንካራ የተማሪ አቴንዳንስ ድጋፍ ለመስጠት አጠቃላይ አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ እንሰራለን። የሚከተሉት የአቴንዳንስ ስርዓታችን ስድስት (6) አካላትን ይገልጻሉ፦

1. የዕለት ተዕለት አቴንዳንስ ልምምዶች
    a. ሁሉም አስተማሪዎች በእያንዳንዱ ክፍል በመጀመሪያዎቹ 10 ደቂቃዎች ውስጥ አቴንዳንስ ይይዛሉ
    b. ተማሪዎች በሚቀሩ ጊዜ እና ምንም የፈቃድ መጠየቂያ ካልቀረበ በ9፡00 ሰዓት ለአሳዳጊዎች እናሳውቃለን።
    c. ስለተማሪ ቀሪዎች ከሁሉም አሳዳጊዎች ጋር እንነጋገራለን።
2. የአቴንዳንስ ቡድን
    a. የት/ቤት አቴንዳንስ አመራር ቡድን የተቋቋመ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ቡድን፦
        i. የትምህርት ቤት አቀፍ የአቴንዳንስ ስር ዓቶችን ለመፍጠር፣
        ii. የስርዓቶቹን ጠንካራ ትግበራ እና ታማኝነት ለማረጋገጥ፣
        iii. የአቴንዳንስ መረጃን ለመተንተን፣ እና
        iv. ሁሉንም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ደረጃ ባለው መልኩ ለዳታ ምላሽ እንዲሰጡ ለመደገፍ የሚሰበሰብ ቡድን ነው።
    b. በ2025-26 የትምህርት ዘመን በሞንትክሌር የአቴንዳንስ ቡድን መሪ ክሊንት ዱቮ (Clint Duvo)፣ ርዕሰ መምህር፣ clint_duvo@dpsk12.net ነው።
3. ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጥሩ አቀባበል ያለው የትምህርት ቤት አካባቢ
    a. በሞንትክሌር፣ ሁሉም ተማሪዎች ሰላማዊነት እና ጥሩ አቀባበል ሊሰማቸው እንደሚገባ እናምናለን። ለትምህርት በአወንታዊ መሰረት ለመደገፍ ቅድሚያ እንሰጣለን፦
        i. እይታዎችን መቀየር (Changing Perspectives)ን በመጠቀም ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርቶችን የመማር እድሎች
        ii. በእያንዳንዱ የክፍል መጀመሪያ ላይ የሰላምታ ልውውጥ ልማዶች
        iii. እንደ አስፈላጊነቱ ለተማሪዎች የግለሰብ ድጋፍ፣ በትምህርት ቤታችን አማካሪዎች፣ ማህበራዊ ሰራተኛ፣ ሳይኮሎጂስት እና ዲኖች ጨምር።
4. ሁለንተናዊ (ደረጃ 1) እንቅስቃሴዎች
    a. ሁለንተናዊ፣ ወይም ደረጃ 1 እንቅስቃሴዎች በሞንትክሌር ያሉ ተማሪዎች እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ያካትታሉ። በ2025-26 የትምህርት ዘመን የሚከተሉትን እናደርጋለን፦
        i. እያንዳንዱ ተማሪ ምን ያህል ትምህርት እንዳመለጠው፣ እና እያንዳንዱ ተማሪ አዘውትሮ ቀሪ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በየወሩ ለሁሉም አሳዳጊዎች እናሳውቃለን።
        ii. ስለአቴንዳንስ አስፈላጊነት ከሁሉም ቤተሰቦች ጋር በመደበኛነት እንነጋገራለን

iii. ጠንካራ አቴንዳንስ ያላቸውን እና አቴንዳንሳቸውን ያሻሻሉ ተማሪዎች በየሦስት ወሩ እውቅና ያገኛሉ።

iv. ለክፍሎች፣ ለክፍል ደረጃዎች እና ለግለሰብ ተማሪዎች የአቴንዳንስ ማበረታቻዎችን እና እውቅናዎችን እንሰጣለን

5. የታለሙ (ደረጃ 2) እገዛዎች
   a. የታለሙ ወይም የደረጃ 2 እገዛዎች አንድ ተማሪ በምክንያት ወይም ያለክንያት መቅረቶችን እንዲሁም እገዳዎችን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት በሞንትክሌር ከተመዘገበው ጊዜ 8-9% ካመለጠው ይከሰታል።
   b. የታለሙ እገዛዎች በሞንትክሌር እና በተማሪው እና በቤተሰቡ መካከል ያለውን አወንታዊ ግንኙነት በማሳደግ ላይ ያተኩራሉ። ይህ ተማሪው የትምህርት ቤት እንቅስቃሴን እንዲቀላቀል መርዳትን፣ ለተማሪው የእኩያ ወይም የአዋቂ አማካሪ መስጠትን፣ ወይም ተማሪው ከሰራተኛ አባል ጋር በዓላማዎች ዙሪያ እንዲገናኝ ማድረግን ይጨምራል።
6. የተጠናከረ (ደረጃ 3) እገዛዎች
   a. የተጠናከረ ወይም የደረጃ 3 ጣልቃገብነቶች አንድ ተማሪ በምክንያት እና ያለምክንያት መቅረቶችን እንዲሁም እገዳዎችን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት በሞንትክሌር ከተመዘገበው ጊዜ 10% ወይም ከዚያ በላይ ካለፈው የሚከሰቱ ናቸው።
   b. የተጠናከረ እገዛዎች ከተማሪው፣ ከቤተሰቡ እና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በመሰብሰብ ከተማሪው ቀሪዎች ጀርባ ያሉ ምክንያቶች ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጀምራሉ። የስብሰባው ዓላማ የአቴንዳንስ ችግርን ለመፍታት መርዳት እና በትብብር የተማሪውን አቴንዳንስ ለማሻሻል እቅድ ማውጣት ነው።

ተማሪዎ በጠንካራ አቴንዳንስ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚያዊ እድገት እንዲኖረው ለማረጋገጥ ከእርስዎ ጋር ለመተባበር በጉጉት እንጠብቃለን!

ስለ ሞንትክሌር አቴንዳንስ ፖሊሲ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎ፣ እባክዎን ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።

Attendance
Every Day Matters